የ Rockbridge ES በድጋሚ የአውራጃ ክለላ ማስታወቂያ **ኖቬምበር 2017 - ፌብሩዋሪ 2018**

የ DeKalb County ት/ቤት አውራጃ በ Stone Mountain እና Clarkston ስብስቦች ውስጥ በድጋሚ የአውራጃ ክለላ ላይ ለመያየት ሶስት የህዝብ ውይይቶችን እያስተዋወቀ ነው፡፡

አዲሱ Rockbridge የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት የቀድሞው የ Wadsworth ጊቢን 2.5 አመት ጊዜያዊ ዝውውርን ተከትሎ በጃንዋሪ 3/2018 እንዲከፈት ተቀጥሯል፡፡ የመጀመሪያው ሙሉ የትምህርት አመት በአዲሱ ቋሚ ጊቢ በፎል 2018 ይጀምራል፡፡

በዚህ አዲስ እና ትልቅ ጊቢ በተገኘው ቦታ አማካኝነት በ Stone Mountain እና Clarkston ስብስቦች ውስጥ የሚገኙ ት/ቤቶች ያለውን የመጨናነቅ ችግር ለመፍታት የመስመሮች በድጋሚ የአውራጃ ክለላ እንዲደረግ አስተያየት ተሰጥቷል፡፡ ይህ በፎል 2018 ስራ ላይ እንዲውል የታቀደው የድጋሚ የአውራጃ ክለላ አስተያየት በእነዛ ስብስቦች ውስጥ ያሉት አጎራባች ት/ቤቶች ላይ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>ተጽዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤቶች፡</u>

- Allgood ES (ከ Clarkston ስብስብ)
- Dunaire ES (ከ Clarkston ስብስብ)
- Hambrick ES (ከ Stone Mountain ስብስብ)
- Indian Creek ES (ከ Clarkston ስብስብ)
- Jolly ES (ከ Clarkston ስብስብ)
- Rockbridge ES (ከ Stone Mountain ስብስብ)
- Stone Mill ES (ከ Stone Mountain ስብስብ)
- Stone Mountain ES (ከ Stone Mountain ስብስብ)

<u>ተጽዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች፡</u>

- Freedom MS (ከ Clarkston ስብስብ)
- Stone Mountain MS (ከ Stone Mountain ስብስብ)

<u>ተጽዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፡</u>

- Clarkston HS (ከ Clarkston ስብስብ)
- Stone Mountain HS (ከ Stone Mountain ስብስብ)

የድጋሚ የአውራጃ ክለላ ሂደቱ ሶስት ዙር ባለው እየጨመረ በሚሄድ በማህበረሰቡ ግብአት የተጀመረ ነው፡፡ አንዴ ሶስቱም ዙር የማህበረሰቡ ግብአት ከተጠናቀቀ በዋና ተቆጣጣሪው የቀረበ የድጋሚ የአውራጃ ክለላ እቅድ ቦርዱ እንዲያጸድቀው በፌብሩዋሪ 2018 ይቀርባል፡፡

ማስታወሻ፡ በሶስቱ ዙር ያለው አስተያየት በሙሉ ከስር በተዘረዘረው የድጋሚ የአውራጃ ክለላ መስፈርት የተገደበ ነው፡

1. ደህንነት እና የትራፊክ ሂደቶች
2. የቀድሞ የድጋሚ የአውራጃ ክለላ
3. ተቀራራቢ ሰፈሮች
4. ልዩ መርሀግብሮች ማለትም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የሚያገለግል፣ ተጨማሪ የመማሪያ ክፍሎች ቦታ የሚያስፈልገው መርሀግበር
5. ከት/ቤት መጋ ጋር መጣጣም
6. ውጤታማ እና አዋጭ ስራዎች

የህዝብ ግብአት፡ ዙር 1 (ኖቬምበር 2/2017 6፡30 PM በ Freedom MS)

የስብሰባው አላማ ከ/ወደ ማህበረሰቡ እንደሚከተለው መረጃ ለመስጠት እና ለመቀበል ነው፡

1. የድጋሚ የአውራጃ ክለላው እንዲደረግ አስተዋጽኦ ያበረከቱ በርካታ ምክንያቶች አጭር መግለጫ
2. ተጽዕኖ ሊደረግባቸው የሚችሉ ት/ቤቶች እና ቦታዎች ዝርዝር
3. የድጋሚ የአውራጃ ክለላው ሂደት እና መስፈርትን አስመልክቶ አጠቃላይ እና የመጀመሪያ ግብአት ከ/ወደ ማህበረሰቡ

ማስታወሻ፡ በዚህ የመጀመሪያ ዙር ስብሰባ ላይ እቅዶች የህዝብ አስተያየት እንዲሰጥባቸው አይደረግም፡፡ የተገኙ አስታየቶች ሁሉ ከሰራተኘው ትንተና ጋር አብሮ በማድረግ ሶስት የድጋሚ የአውራጃ ክለላ አማራጮች ይዘጋጀል፤ ይህ ለህብረተሰቡ ቀርቦ በሁለተኛው ስብሰባ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

የህዝብ ግብአት፡ ዙር 2 (ኖቬምበር 30/2017 6፡30 PM በ Clarkston HS)

የዚህ ስብሰባ አላው ለድጋሚ የአውራጃ ክለላ ሶስት አማራጭ ለማቅረብ እና በእያንዳንዱ አማራጭ የተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የማህበረሰቡን ግብአት/አስተያየት ለማግኘት ነው፡፡

ማስታወሻ፡ በሁለተኛው ዙር ስብሰባ የተገኙ አስተያየቶች ለድጋሚ የአውራጃ ክለላ አንድ በሰራተኛ የቀረበ አማራጭ ለማዘጋጀት ይረዳል፤ ይህ ለህብረተሰቡ ቀርቦ በሶስተኛው ስብሰባ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

የህዝብ ግብአት፡ ዙር 3 (ጃንዋሪ 11/2018 6፡30 PM በ Rockbridge ES)

የ Rockbridge ES በድጋሚ የአውራጃ ክለላ ማስታወቂያ **ኖቬምበር 2017 - ፌብሩዋሪ 2018**

የዚህ የሶስተኛ እና የመጨረሻ ዙር አላው ለድጋሚ የአውራጃ ክለላ ሶስት አማራጭ ለማቅረብ እና በዚህ አማራጭ ላይ የማህበረሰቡን ግብአት/አስተያየት ለማግኘት ነው፡፡

ማስታወሻ፡ የቀረበው አንድ አማራጭ በዙር ሁለት ላይ የቀረበውን አንድ አማራጭ ያንጸባርቃል ማለት አይደለም፡፡ እንደውም ይህ አማራጭ ከዙር አንድ ወይም ሁለት የተሰባሰቡ የሁሉም የህዝብ አስተያየቶች እንዲሁም የሰራተኞች ትንተና ውጤት ይሆናል፡፡ ይህ አንድ አማራጭ ከቀረበ በኋላ ሊሰራበት የታቀደውን እቅድ የተናጠል ሁኔታዎች አስመልክቶ የማህበረሰብ ግብአት ይከተላል፡፡ ይህ እቅድ የመጨረሻ አይደለም፡፡

በዋና ተቆጣጣሪ የቀረበ የድጋሚ የአውራጃ ክለላ እቅድ

ከሁሉም የማህበረሰብ ግብአት (በተለይ የቅርብ በሰራተኛ የቀረበ አማራጭ) ዙሮች የማህበረሰብ አስተያየት ከተገኘ በኋላ ዋና ተቆጣጠሪው አስፈላጊውን ማንኛውም ለውጥ ያደርግ እና በዋና ተቆጣጣሪ የቀረበ የድጋሚ የአውራጃ ክለላ እቅድ ቦርዱ እንዲያጸድቀው ያቀርባል፡፡

ቦርድ የሚያጸድቀው (ፌብሩዋሪ 2018)

ቦርዱ እንዲያጸድቅ የሚጠበቀው ፌብሩዋሪ 2018 ሲሆን ማንኛውም የቦታ ማስተካከያ የሚጀመረው ፎል 2018 ነው፡፡

ለተሟላ ዝርዝር እና መረጃ እባክዎ www.dekalbschoolsga.org/redistricting ይጎብኙ፡፡